# የአማራው መደራጀት የተጋረጠብትን እሾኮች መንቀል መቻል አለበት

November 7, 2016




(አብነት ሁነኛው)

ፋሺስቶችና አምባገነን ዘረኞች ከጥንት አንስቶ የሚያመሳስላቸው አንድ ነጥብ አለ፡ እርሱም ታሪካዊ ጠላቴ ነው ብለው የፈረጁትን ማህበረሰብ(ነገድ፤ብሔረሰብ፤ጎሳ) ነጥለው ሁለገብ ጥፋት እንዲደርስበት ባለና በሌለ ሀይላቸው መምታትና ማስመታት ነው። ዛሬ በቱርክ፤በኢራን፤በኢራቅ፤በሶሪያ ተበታትኖ ቁምስቅሉን የሚያየው የኩርድ ሕዝብ እንደዚሁም በመካከለኛው ምስራቅ አገር አልባ እንዲሆን ሲወርድ ሲዋረድ የ ተፈጠረበትን ጉልት ያጣው የፍልስጤም ማህበረሰብ ወዘተ. ተጠቃሽ ምሳሌዎች ናቸ ው። ታድያ ወደ ኢትዮጵያ ስንመለስ በተለይም ሕወሐትና አክራሪ ግራ ዘመም ጎጠኞ ች ከፍ ብለው ከተጠቀሱት ሕዝቦች ተራ እንዲመደብ ወስነው ከስር መሰረቱ እንዲመ ሳቀል የሸረቡበት የአማራው ነገድ ለመሆኑ ምንም ጥርጥርና ሙግት የማያሻው የወቅ ቱ ሀቅ ነው።

ለነዚህ መሰሪ የአማራ አጥፊ ሀይሎች ደግሞ የአውሮፓዊያን ጉልበተኞች በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ጣልቃ በመግባት፤ ሸር በመጎንጎን፤ አጎብዳጅነት የሚያጠቃቸው መ ሪዎች ያሉዋቸውን ጎሳዎች በመያዝ በታሪክ አማራውን አስጨፍጭፈዋል። በዮዲት ጉዲት ዘመን የውጭ አይሁዶችን ግፊት የተመረኮዘችው ጨካኝ ንግስት በአመዛኙ በተንቀሳቀሰችባቸው የሰሜን ኢትዮጵያ አካባቢዎች ጄኖሳይድና የንብረት እንደዚሁም የቅርስ ውድመቶችን ያካሄደችው ክርስትያን ነው ብላ በደመደመችው የአማራ ሕዝብ ላይ ነበር። በ እርስዋ እግር የተተካው ግራኝ አህመድ ደግሞ በኦቶማን ቱርኮች ልክፍ ት ተይዞ በጅሀድ መልክ በአማራው በተለይም በሸዋ ክርስትያኖች ያደረሰው ጭፍጨ ፋና የአብያተ ክርስትና ቅርሶች ጥፋት በከፈተው በር ዘው ብለው በገቡት የተለያዩ የ ኦሮሞ ሉባዎች አማራው ለደረሰበት የዘር ማጽዳት ወንጀልና የስር መሰረት የመሬት ጉልቱን በግፍ እንዲቀማና የበይ ተመልካች እንዲሆን እንዳጋለጠው ከበርካታ የታሪ ክ ማስረጃዎች እንረዳለን።

ብዙ ርቀን ሳንጉዋዝ በ 19 ነኛው መቶ ክፍለ ዘመን አጼ ቴዎድሮስ አገሪቱን አንድ አደ ርጋለው ብለው ሲነሱ እንግሊዞች በቀይ ባህር፤ በንስር(ግብጽ) ና ሱዳን ላላቸው የቅኝ አገዛዝ ችግር ሊፈጥር እንደሚችል በመገንዘባቸው "ዜጎቼን አሰረብኝ" በሚል ሽፋን ንጉሱን ለማንበርከክ የተወዳጁት ካሳ ምርጫ ወይም በሁዋላ አጼ ዮሀንስን በትግራይ በኩል ልክ አይሁዶቹና ኦቶማኖቹ በጉዲትና በግራኝ እንደተጠቀሙባቸው አገልጋያቸ ው ማድረግ በመቻላቸው እንደነበር ክርክር መግጠም አያሻም፡፡ ጣሊያንም በተለያዩ አጋጣሚዎች ኢትዮጵያን ስትወር አብላጫው ጦርዋ የተውጣጣው ከሀማሴን፤ አካለ ጉዛይ፤ ሰራዬ፤ አዲግራት፤ አድዋ፤ ተምቤን ወዘተ. ከመለመለቻቸው ትግሬዎች የተው ጣጡ እንደነበርም ራሳቸው ጣልያኖቹ ከጻፉዋቸው ሰነዶች የምናገኘው የማይደበቅ አሳ ፋሪ ሀቅ ሲሆን፡ ወደድንም ጠላንም ይህ የታሪካችን ጥቁር ጠባሳ ለመሆኑ ምንም ዓይ ነት ጥርጣሬ ሊገባን አያስፈልግም።

አሁን ላይ ጠባብና አደገኛ የሆኑ ዘረኞች ኢትዮጵያን ለመበታተን የሚጠቀሙባቸው አካሄዶች በተለይም ወያኔና ኦነግ የሚመሩት ጣልያኖችና ጀርመኖች ጎንጉነው በተው ላቸው ትንተናዎችና ካርታዎች ላይ ተሞርኩዘው ሲሆን ለዚህም የአፍራሽ ጥንስስ እ ውን መሆን ደግሞ እነዚሁ ቅኝ ገዢ አውሮፓዊያኖች አገሪቱን ለመበታተንና እንዳፈ ለጉት ጥቢጥቢ መጫወቻቸው ለማድረግ እንቅፋት የሆነባቸውን አማራ ለማስመታት ባሰመሩላቸው መንገድ እንደሚንቀሳቀሱ ከድርጊቶቻቸው መገንዘብ ይቻላል።

ወጣም ወረደ አማራው የቁምስቅሉን ማየት የጀመረው ከዮዲት ግዜ አንስቶ ቢሆንም በታሪኩ የከፋና ሊጠፋ እስከሚችል ድረስ ሁለገብ የሆነ ማለትም ፖለቲካዊ፤ኢኮኖሚ ያዊ፤ባሕላዊና ማህበረሰባዊ ውድመቶች እየደረሱበት ያለው ግን ሕወሐት ስልጣን ከ ጨበጠበት ከ 1983 ዓም. ጀምሮ እንደሆነ መላው የአማራ ተወላጅ እየቀመሰው ያለ የጥፋት ጽዋ

ነው ቢባል ማጋነን አይሆንም። ይህ አማራ የሚባለው ነገድ የለህም ከሚ ለው ፕሮፓጋንዳ አንስቶ ቤተስኪያን እንደገባች ውሻ ጭንቅላቱን ያልተመታበት አንዲ ት ቀን ባሳለፍነው 25 ዓመት ውስጥ አለን? መልሱ ጨርሶ የለም ነው። ”ውሀ ሲወስድ እያሳሳቀ ነው. . .” እንደሚባለው ”በክልል ደረጃ አገር ሰጥተንሀል፤ ነገ ርግን መደራጀት ስለማይገባህ እኛ ወያኔዎች አገልጋያችንን ብ አ ዴ ንን ወደ መጨረሻ የጥፋት ገደል እንድትገባ ጭነንበሀል” ብለው በታሪኩ እንዳይኮራ፤ በማንነቱ አንገቱን እንዲደፋ፤ ወልዶ ከብዶ ዘሩን እንዳይተካ፤ በልማት ተረስቶ በድህነት እንዲማቅቅ፤ በደማላትና አጥንቱን በከሰከሰባት አገሩ መጤ ተብሎ እንደተክለፈለፈች ውሻ ተቅበዝ ብዞ መግቢያና መውጫ አጥቶ ኑሮውን በተደራረበ መከራ እንዲገፋ፤ በመላው የአገሪቱ ክልሎች እንዲጨፈጨፍና ደሙ ደመ ከልብ እንዲሆን፤ ከዛችው ሰጥተንሀል ከተባለችው ቁንጽል መሬት በአዊ፤ በዋግ፤ በኦሮሞ፤ በአርጎባ፤ በቅማንት ወዘተ.ተከፋፍሎ፤ የተረፈውን ደግሞ ለትግሬዎች ትልቅነትና ለሌሎች ኩታ ገጠም ክልሎች በየግዜው ተሸንሽኖ እየተ ወሰደበት ህልውናውንና መኖሪያውን እንዲያጣ ወዘተ.. ተፈርዶበት ያለና አይዞህ አለሁ ልህ የሚለው ሳይኖረው መሪውን ያጣና የተበተነ የንብ መንጋ ሆኖ ይገኛል።

በአንድ ወቅት በአማራው ላይ የመጣውን የጥፋት መከራ የተገነዘቡት ፕሮፌሰር አስራት ነብሳቸውን ይማርና የመላው አማራ ሕዝቦች ድርጅትን ቢመሰርቱም በጉልበተናውና እ ብሪተኛው ወያኔ ያላሳለሰ የጥላቻ ዘመቻና የአማራ ምሁራን ነን በሚሉ ግለሰቦች ተቃው ሞ ሲፈርስ ይህ ታሪካዊ ጀግና ማህበረሰብ የሚያነቃው፤ የሚያደራጀው፤ አይዞህ የሚለ ው ድርጅት አልባ ሆኖ ወያኔና አጋር ድርጅቶች የሚባሉት ሲጨፍሩበትና ሲመቱት ወ ይም በዘመኑ አገላለጽ ሰብዓዊና ዲሞክራሲያዊ መብቱን ገፈው እንደ ሁለተኛ ዜጋ ሲቆ ጥሩት ማንም የሚደርስለት በመጥፋቱ የሁኔታውን አሳሳቢነት የተረዳ አማራ ከአገር ቤት ”አስቸኳዋይ ጥሪ ለአማራ ተወላጆች በሙሉ” በሚል ባልሳሳት የዛሬ 4 ወይም 3 ዓመት በዘሐበሻ ያወጣውን የብሶትና በደል ገድል የሚያስታውስ ካለ ”ዛሬ አማራው ተበድሎ ስለሚገኝ እንሰባሰብ” ብለው ለተነሱት የአማራ ወጣቶች መሰረት ሊሆን ስለሚችል በ ወልቃይትና ሌሎች አማራውን በሚያጎሉ ድህረገጾች በድጋሚ ወጥቶ ለንባብ ቢበቃ በ ጣም ይጠቅማል የሚል ሀሳብ አለኝ፡ በነገራችን ላይ ሞረሽ የተመሰረተው ይህ ጽሁፍ ከወጣ በሁዋላ ሲሆን የሁኔታው መገጣጠም ደግሞ ለአማራው በማንነቱ ለመሰባሰብ ደንዝዞ የነበረውን አመለካከት ለውጦታል ለማለት ያስችላል።

የአማራው በማንነቱ መደራጀት ከእንግዲህ ወዲያ በተአምር የሚቀር ጉዳይ አይደለም። በተከታታይ በኢሳት፤ በኢትዮ ቲዩብ፤ በአባይ ሚዲያ፤ በሕብር ራዲዮ ወዘተ... ስለ አማ ራው መደራጀት የቀረቡትን ቃለ መጠይቆችን ተከታትያለሁ፡ በጣም ያስገረመኝ ጠያቂዎቹ ተመሳሳይ በሆነ መልኩ የአማራው በማንነቱ መደራጀት ለአንድነት ጠንቅ እንደ ሆነ አድርገው በማቅረብ ሲከራከሩ መገንዘብ የቻልኩት አማራው እያለቀና እየተመታ በርሱ መቃብር ላይ አንድነትን ማስቀጠል ያስፈልጋል፡ ሌሎች ጎሳዎች ግን በማንነታቸ ው ቢደራጁና ራሳቸውን ቢያጎለብቱ ግድ የለንም አይነት አቁዋም እንደያዙ መሆኑን ነው። (ከአባይ ሚዲያ ጠያቂ በስተቀር)
በጣም የሚያሳዝን ነገር ነው፡ ምክንያቱም እንዴት አማራ ተደራጅቶ ከደረሰበት ጥፋት ራሱን ያድን ወይም ከጭፍጨፋ ድኖ ከሌሎቹ ጋር በጋራ አንድነትን ያጠናክር የሚለው ን ሀሳብ እንኩዋን ማጤን አለመቻላቸውና ”በቡሀ ላይ ቆሮቆር” እንደሚባለው በማንነቱ ብቻ የሚመታው አማራ ላይ የሞት ፍርድ እንደመፍረድ የሚቆጠር ሆኖ አግኝቼዋለው። ከዚህ ጉድ ጋር ተዳብሎ የአማራውን መደራጀት ከመፈታተን አልቆጠብ ያለው በተለይ ም ከአገር ቤት ከወጡ በርካታ ዓመቶች ያስቆጠሩትና በአንድነት አስተሳሰብ የታወሩት ምሁሮች አማራው ላለፉት ሩብ ክፍለ ዘመን በግፍ ሲጨፈለቅና ሲበታተን ከጎኑ ሊቆ ሙለት ካልቻሉ ስብስቦች ጋር በጭፍን ወግነው እውቀታቸውን፤ ግዜያቸውንና ገንዘባ ቸውን በማፍሰስ የመተመዳቸው ግትር አባዜ ነው። አንድነትን እኔ እስከማውቀው አን ድም አማራ የሚቃወም የለም፡ ”ምን ይዞ ጉዞ” እንደሚባለው ኢትዮጵያና አረንጉዋዴ ቢጫ ቀይ አማራው ለማንም አሳልፎ የማይሰጣቸው መገለጫዎች ናቸው። በዚህ ታሪ ካዊ ስነልቦና በደሙ ውስጥ ሰርጾ ያለውን አማራ እንዲደራጅ ከመቃወም ያለምንም ማ መንታት ቢደግፉት የአንድነቱ ጎራም ምሰሶና የጥንካሬ መሰረቱ ሊሆን እንደሚችል ያል ተገነዘቡበት ምክንያት አይገባኝም።

አሁን ላይ የምሰማው ግን ከነዚህ ሚዲያዎችና አንዳንድ ምሁራን በከፋ ለአማራው የራስ አድን የመደራጀት ጉዳይ ላይ ጥቁር ነጥብ የሚያጭሩ የዚህና የዚያ ”ህብረት” በሚል እየ ተመሰረቱ ያሉና ወያኔ አማራውን ለማጥፋት በሚያደርገው ሩጫ እንዳይዳከም ፎጣና ውሀ ለማቅረብ እየተንቀሳቀሱ ያሉ ስብስቦች ምንነትና ግልጽ ያልሆነ አላማቸው ነው። በጎንደርና በጎጃም ያለው ሕዝብ ጎንደሬ ወይም ጎጃሜ ተብሎ አይደለም በአጋዚጨካኞ ች የሚገደለው፡ ”አማራ ነህ” ተብሎ እንጂ፤ የወልቃይት ጥያቄ እኮ ”ጎንደሬ ነኝ” የሚል ሳይሆን ”የአማራ ማንነት” ጥያቄ ነው፡ ከተሳሳትኩ ልታረም ዝግጁ ነኝ። በወሎም በኩል እንደዚሁ ”ህብረት” ተመሰረተ የሚል ዜና ሰምቻለሁ፡ ለመሆኑ እነዚህ ”ህብረት” የሚባ ባሉት በደቡብ፤ በኦሮሚያ፤ በጋምቤላ፤ በመተከልና ቀማሺ፤ በኢጋዴን፤ በራሱ የአማራ ክልል በሚባለው ሲጨፈጨፉና አገርህ አይደለም ተብለው ባዶ እጃቸውን ሲባረሩ የት ነበሩ?

በሀቅ እንነጋገር ከተባለ ወገኖቻችን እፍዳው የወረደባቸው ጎንደሬ ወይም ጎጃሜ ወዘተ ተብለው ሳይሆን መጤ፤ ትምክህተኛና ጽንፈኛ አማራ በሚል ተፈርጀው አይደለምን? ባንድ ወቅት ትዝ ካላችሁ የወያኔ ፓርላማ ውስጥ የበፊቱ የሕወሐት ጠቅላይ ሚኒስትር ”ከጉራ ፈርዳ አማራዎች አልተባረሩም ከመካከላቸው የተወሰኑት ግን በደን ምንጠራ

ወንጀል ተሰማርተው ስለነበር ወደመጡበት እንዲመለሱ ተድርገዋል፡ አብዛኞቹ አሁን ም እዛው ይኖራሉ እንዲያውም አመራር ላይም ያሉት እነርሱ ስለሆኑ ባጭሩ አካባቢው ሌላኛው ምስራቅ ጎጃም ሆን ዋል ማለት ይቻላል።" ብሎ በቅጥፈት የዘር ማጥፋት ወን ጀሉን ሲያድበሰብሰውና ከወለጋ እስከዛሬ ድረስ ከጎጃም አካባቢ የፈለሱ በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ አማሮች ሲሙቱና ሲባረሩ ወዘተ. ዛሬ በ ጎጃም ህብረት ተደራጀን የሚሉት ሰዎች ከዝምታ ውጪ ምን የፈየዱት ነገር ነበር? ትግሬዎች በማን አለብኝነት አብጠው ወልቃይትን፤ ጠገዴንና ጸለምትን በ ተጨማሪም ከቡሀይት ወረዳ አንድ ቀበሌ ሲቀሙ ወዘተ. ለሱዳንም ከቋዋራና መተማ እንዲሁም አርማጭሆ መሬት ሲለግሱ የጎንደር ህብ ረት እጁን አጣጥፎ ከመቀመጥ ሌላ ያደረገው ፋይዳ ይኖር ይሆን?

ዛሬ ላይ አማራው የጋረደውን ዓይነጥላ አስወግዶ ለመሰባሰብና ማንነቱ እንዳይጠፋ ለ መደራጀትና ለመታገል ሲያኮበክብ፤ በአማራ ማንነት ጥያቄ ጎንደርና ጎጃም ሲታመሱና በዛም ያሉት ወጣቶችና ገበሬዎች አሁን ላይ ደግሞ ነጋዴዎች በእርኩሱ ኢጋዚና ደህንነ ቶች የጥይት እራት ሲሆኑ የተረፉት ደግሞ በየስርቤቱ ታጉረው ሲወገሩ የህብረቶቹ ፍ ላጎት በጎንደሬነትና በጎጃሜነት እንጂ በአማራነት ከታገልክ መከራው ይበዛብሀል ስለዚ ህ አማራነትን እርሳው ወደማለት የሚያደሉ ይመስላሉና "አያ ጅቦ ሳታማህኝ ብላኝ" ዓይነት እንዳይሆን አማራነትን መቀበል ክብር እንጂ ውርደት ስላልሆነ ወደ መደራጀቱ ጎራ ከመዝለቅ ሌላ ከጥፋት የመዳኛ አማራጭ አይኖርም።

አጥፍቶ ጠፊ የሚመስልና ሕዝብን በሰፈር ብቻ አሳንሶ ለማደራጀት ህብረት ነን የሚሉ ት በዚች አንድ ዓመት ውስጥ መረባረብ የጀመሩበት ምክንያት የተወሳሰበ ቢመስልም ቀንደኛው ዓላማቸው ግን አማራው በማንነቱ እንዳይደራጅ ደንቃራ ለመሆን ስለመታ ሰቡ ግን ምንም ጥርጥር የለውም። ለመሆኑ በነዚህ ሁሉ ተንኮሎች ውስጥ የወያኔ ትግ ሬዎች ተንኮል ይኖርበት ይሆን? ይህን የምጠይቅበት ምክንያት ሕወሀት አማራው ፈጽ ሞ እንዲደራጅ እንደማይሻ ስለማውቅና ከፍተኛ ገንዘብ በመስጠት ወይም በመክፈል ዓላማውን ለማራመድ ቀዳዳዎችን አፈላልጎ እንደሚገባ አገር ቤት ውስጥ በሰላም እን ታገላለን ከሚሉት ፓርቲዎች ስንቶቹን እንደከፋፈላቸውና እንዳወደማቸው ሁላችንም የምናውቃቸው በርካታ ማስረጃዎች ስላሉ ነው።

"ጉድና ጭራ ከበስተዋላው" እንደሚባለው የነዚህ "ህብረት" የሚባሉት ሚስጢርም ግዜውን ጠብቆ ይወጣልና ለአማራው ተደራጅቶ የመታገሉ ሀቅ ግን መሬት ከፍ ሰማይ ዝቅ ቢሉ አይቀሬ ስለሆነ አማራው በርታ፤ ጆሮህን ለቀልባሽ አትስጥ፤ "ከራስ በላይ ነፋስ" ይባላል፡ ሁሉም ቤቱን በሚያደራጅበት ወቅት አንተም ሳትዘናጋና የተከፈተብህን የፕሮፖጋንዳ ጦርነት ሀግ ብለህ በ አማራ ማንነትህ ተደራጅ፤ ተሰባሰብ፤ አንቅተህ ንቃ፤ ታጥቀህ አስታጥቅ፤ ይሉንታን አሽቀንጥረህ በመጣል አስቀድመህ የራስህን ቤት አሙቅ። ሌሎቹ "ቻርተር" ቅብንጥርሶ እያሉ በብዙ ነገሮች አማራውን ጥለውትና አልፈውት ተጉ ዘዋል፡ ነገና ተነጎድያ አደጋው አሁን አማራው ካለበት ጥፋት በበለጠ ጥርሱን አግጦ ሳ ይመጣና የአማራው ነገር "ሰርገኛ መጣ በርበሬ ቀንጥሱ" እንዳይሆን ያሉትን የመደራጀት ስንኩሎችና ደንቃራዎች ስልታዊ በሆነ ሁኔታ በማንጉዋለልና ከአማራ የመኖርና አለመኖ ር ጉዳይ ማንም አይበልጥም በሚል የማያወላውል ጽናት ላይ ቆመን አማራዎች ነን የም ንል ሁሉ አንድ መላ ባስቸኩዋይ መፍጠር ይጠበቅብናል።

**አብነት ሁነኛው ነኝ!!!**